መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

# የጳውሎስ አስደናቂ ጉዞ፡፡



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

የኢየሱስ አገልጋዮች ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ውስጥ ነበሩ፡፡ በፍጹም! ያጠፉት ነገር የለም ፤ ከአንዲት ሴት ላይ አጋንንት አስወጥተው ነበረ፡፡ የኃያሉን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚያመልኩ በፊሊጲስዩስ ላሉት ጣኦታትን አሳይተዋቸው ነበረ፡፡ በዚህም ምክንያት በር ተዘግቶባቸውና ታስረው ያለቅሱ ነበረ፡፡





ጳውሎስና ሲላስ በዚህ
ምክንያት አዝነው ይማረራሉ
ብለህ ታስብ ይሆናል፡፡ ነገር
ግን እንደዛ አልነበሩም፡፡
በእርግጥ ፣ በሌሊቱ መካከለኛ
ሰዓት ለእግዚአብሔር ዝማሬን
እየተቀኙ ነበረ ፤ በዚያ በእስር
ያሉ ሁሉ ይሄንን ይሰሙ ነበረ፡፡

በድንገት ፣ ዝማሬው ቆመ፡፡ እግዚአብሔር ወሕኒውን የሚያናውጥ የምድር መናወጥን ላከ፡፡ በሮች ሁሉ ተከፈቱ፡፡ የሁሉም እስራት ተፈታ፡፡





ኦ! ኦ! በግርግሩ መሐከል ታሳሪዎቹ ሁሉ እንዳመለጡ ፤ አሳሪው እርግጠኛ ነበረ።። አንዱ እንኳን ቢያመልጥ ፤ አሳሪው በሞት ይቀጣ ነበረ።። በአሳዛኝ ሁኔታ ፤ አሳዛኙ አሳሪ ሰይፉን መዘዘ ፤ ራሱን ሊገድልና ሊገላገል ነበረ።።

ነገር ግን ጳውሎስ ተጣራ ፣"
በራስህ ላይ አንዳች ክፉ
አታድርግ ፤ ሁላችንም በዚህ
አለን፡፡" አሳሪው ያንን ሲያይ ፣
እንዲህ አለ ፣ "እኔ ለመዳን ምን
ማድረግ አለብኝ;" እነርሱም
እንዲህ አሉት ፣ "በኢየሱስ
ክርስቶስ እመን ፤ አንተም
ቤተሰብህም ትድናላችሁ፡፡"
በደስታም ፤ አሳሪው አመነ፡፡





በቀጣዩ ቀን ተፈተው ፣ ጳውሎስና
ሲላስ በብዙ የተለያዩ ከተማዎች
እየተዘዋወሩ ስለ ኢየሱስ ተናገሩ፡፡
አንዳንዶች አመኑ ፤ ሌሎች
ሊጎዷቸው ሞከሩ፡፡ ነገር ግን
እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋ
ነበረ፡፡ አንድ ምሽት ፣ ጳውሎስ
ለሰዓታት ይሰብክ ነበረ፡፡ አንድ
ጎበዝ በተከፈተ መስኮት በኩል
ተኝቶ ነበረ፡፡ከዚያ ምን
እንደተፈጠረ ማሰብ ይቻላል፡፡



ያ ጎበዝ እንደሞተ ሁሉም
ሰው አወቀ። ነገር ግን
ጳውሎስ ሔደና አቅፎት
እንዲህ አለ ፤ “ሕይወቱ
በእርሱ ውስጥ አለች።”
ያንንም ጎበዝ በሕይወት
እንዳለ አመጡት ፤ እነርሱም
እጅግ ደስተኛ ነበሩ።

ጳውሎስና ሲላስ በአውሮጳ ሲዘዋወሩ ፣ ብዙ አስደማሚ ጊዜአት ነበሩአቸው፡፡ አንደኛው የጳውሎስ አስደማሚ ጊዜ በመርከብ ሳለ የተከሰተ ነው፡፡ እነዚህ መርከቦች የተሳፋሪዎች መርከብ አይነት አይደሉም ፤ ይልቁንም የንግድ ጀልባዎች ናቸው ፤ በቀላሉ ማዕበል ባለበት ስፍራ ሊሰጥሙ የሚችሉ፡፡





ጳውሎስ ዳግም በመታሰሩ ምክንያት በመርከቡ ውስጥ ነበረ፡፡
የዓለም ታላቋ ከተማ በሆነችው በሮም ንጉስ ፊት መቅረብ ነበረበት፡፡
ታላቅ ንፋሳት መርከቢቱን ያቀዘቅዙት ጀመረ፡፡ ማዕበል ያለበት የአየር
ንብረት እንደሚጠብቃቸው የሚያመላክት ነበረ፡፡ ለጳውሎስና ለሌሎች
ተጓዦች እጅግ አስቸጋሪ ጉዞ ነበረ ፤ ለቡድኑም በአጠቃላይ፡፡

ጳውሎስም እንዲህ ብሎ አስጠነቀቀ ፣ "ሰዎች ፣ ይሔ ጉዞ በአደጋ ነው የሚጠናቀቀው።" ካፒቴኑ ግን አልሰማቸውም ነበረ። በባሕሩ ውስጥ ሔዱ። ትልቅ አውሎ ነፋስም ሲመታቸው ፣ ከመሰባበር ለመከላከል ፣ በመርከቡ ዙሪያ ገመድ አሰሩ። መርከቡ ቢሰበር ፣ ለሁሉም ውኃማ መቃብር ይሆናል።



መርከቢቱ መናወጥ ጀመረች ፤ ካፒቴኑ እቃ እያወጡ የማቅለሉን ስራ
እንዲያግዙት ለሁሉም ጥሪ አቀረበ። በሶስተኛው ቀን ፤
የመርከቡን መልሕቅ በባሕሩ ዳርቻ ላይ ተከሉ።
ምንአልባት ይሔ ይረዳቸው ይሆናል።



በማታ ክፍለ ጊዜ ፣ አንድ መልዓክ በጳውሎስ በኩል ቆሞ ፣ ሁሉ ነገር መልካም እንደሚሆን ነገረው።
ሌሎቹም ጳውሎስ “ልባችሁ አይውረድ ፤ ሰዎች ፣ እግዚአብሔር እንደተናገረኝ እንደሚሆን አምናለሁ። ነገር ግን የሆነ ደሴት ላይ እንደርሳለን።



ከጥቂት ቀናት በኋላ ፣ ጀልባይቱ መላጢያ
ወደ ሚባል ደሴት ተቃረበች፡፡ ከቋጥኛጋ
ተጋጭታ ተሰባባረች፡፡ ካፒቴኑም መዋኘት
የሚችሉትን ከመርከቢቱ ውስጥ እንዲወጡ
አዘዛቸው፡፡ የተቀሩትም በደሕና ደረሱ ፣
አንዳንዶቹ በወደቡ ላይ ዋኝተው ደረሱ
አንዳንዱ ደግሞ በመርከቢቱ ውስጥ ሆኖ፡፡



በመላጢያም እግዚአብሔር ኃይሉን ገለጠ።
ለእሳት የሚሆን እንጨት ሲሰበስቡ ፣ እፉኝት
ወጥታ ጳውሎስን ነደፈችው። ነገር ግን
የእፉኝቱ ንድፊያ ጳውሎን አልጎዳውም ነበረ።
ሰዎቹም ይሄንን አይተው ጳውሎስን አምላክ
ነው አሉ። ብዙ ታማሚዎችም መጡ ፤
ጳውሎስም ከጸለየላቸው በኋላ
እግዚአብሔር ፈወሳቸው።



በመጨረሻም ጳውሎስ በሮም ደረሰ፡፡ የእርሱ ጉዳይ በፍርድ ቤት እንዲሰማ ወደ ሁለት አመት የሚሆን ጊዜ ወስዶበት ነበረ፡፡ በዚያን ጊዜ፣ ጳውሎስ ቤት ተከራይቶ እንግዶችን ይቀበል ነበረ፡፡ ጳውሎስ ለእንግዶቹ ምን ይናገር እንደነበረ ታውቃለህ; የእግዚአብሔርን መንግስት ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን !



ጳውሎስ በሮም የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበረ ፤ ልክ እንደሌላ ጉዞዎቹ ሁሉ፡፡

ጳውሎስ ከሮም ሆኖ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ ፤ ሐይማኖትን ጠብቄአለሁ፡፡" እያለ ይጽፋል፡፡ ሕይወቱ እንዴት እንደተጠናቀቀ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም ፤ ነገር ግን ሌሎች ሰነዶች እንደሚያሳዩት ጳውሎስ በንጉስ ኔሮ ትዕዛዝ ጭንቅላቱ ተቀልቶ እንደሞተ ነው፡፡ ጳውሎስ እንደኑሮው ነው የሞተው ፤ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ፤ ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮ፡፡



የጳውሎስ አስደናቂ ጉዞ።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የሐዋርያት ስራ 16 ፣ 27 ፣ 28

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16